# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

# UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

## የአዲስ አመት የነፃነት የትግል ጥሪ!

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የተነጠቀውን ነፃነቱን

## ለመቀዳጀት ዛሬውኑ ለትግል ይነሳ!

ሀገራችን የረጅም ዘመን ገናና ታሪክ ባለቤት ብትሆንም ሕዝቧ ግን በአፈና አገዛዞች ሥር ሲማቅቅ አያሌ ዘመናትን አሳልፏል። የሩቁን ዘመን ትተን ዘመናዊውን የሀገራችን ታሪክ ብናይ ከታህሣሥ 1953 ዓመተ ምህረት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት ለመሆን የጀመረው ሁሉን አቀፍ ትግል ይኸውና ዘንድሮ 2003 ዓም ታህሣሥ ወር ሃምሳ ዓመት ሞላው።

የሃምሳ ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል ቢያደርግም እንደአለመታደል ሆኖ ነፃነቱን በመጎናፀፍ ፋንታ ከአብራኩ የተቀፈቀሀፉ አምባገነኖች አንዱን ያዘለበት የጀርባው ቁስል ጠፈፍ ሳይል ሌላው እየተተካ ዘመኑን ሁሉ በዋይታና በሰቆቃ ማሳለፍ ግድ ሆኖበታል። ሁልጊዜም ተስፋን ለሕዝብ ባልሰነቁ ነገር ግን በአፈና ችጋር የታጨቁ ዓመታትን 365 ቀናትን እየቆጠረ ይቀበላል። ይሸኛል። አንዱን አምባገነን በጽኑ ትግል ከጀርባው ያወርዳል፣ ሌላውን ከመቅጽበት ያለፈቃዱ ያዝላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለፉት ሃምሳ ዓመታት ሁኔታ ይኸን ይመስላል። ከሃምሳ ዓመታቱ ውስጥ ግማሽ ያክሉን ሕዝቡን ረግጦ እየገዛ ያለው የኢህአዴግ አገዛዝ ነው።

ይህ አገዛዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ አፍኖ እየገዛ የሚቀጥልበት አንዳች ሞራላዊ ምክንያት የለውም። በተግባር ሕዝብን የመምራት አገርን የማልማት አንዳች ብቃት እንደሌለው በተደጋጋሚ አሳይቷል። የአገዛዙ ቁንጮ እንዳሉት በጥፍርና በጥርስ ምን እያደረጉ አገር እንመራለን እያሉ እየተፍጨረጨሩ ነው። ይኸን አገዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕጋዊና ሠላማዊ ትግል በማድረግ በቃህ ሊለው ሕዝቡም የስልጣኑ ባለቤት ሊሆን ይገባል። የኢትዮጵያም ሕዝብ ለሃምሳ ዓመታት ያለ አስተማማኝ ውጤት የደከመበት የነፃነት ትግል ለፍሬ ሊበቃ ይገባል። በኢትዮጵያ የአመባገነኖች አዙሪት ሳይውል ሳያድር ሊቋጭ ይገባዋል። የኢትዮጵያም ሕዝብ ታሪኩንና ማንነቱን የሚመጥን መዘውሩን በቅጡ የሚቆጣጠረው መንግሥት ይኖረው ዘንድ የግድ ነው።

የ2004 ዓም እንዳለፉት ሃምሳ ዓመታት የጨለማ ዓመታት ሆኖ ሊቀጥል አይገባውም። ለሁለንተናዊ ነፃነት ሁሉን አቀፍ የነፃነት ትግል የሚደረግበት አመት ሊሆን ይገባዋል። የሚደረገው የነፃነት ትግልም ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ለኢህአዴግ አባላትም ጭምር ነፃነትን የሚያጎናጽፍ ሊሆን ይገባዋል። ትግሉ ከዘረኝነት ከበቀልና ከቁርሾ የፀዳ ሁላችንንም ኢትዮጵያውያንን ከሊቅ-እስከ ደቂቅ የሚያስተባብር አንድነታችንን ከመቼውም ጊዜ በላይ ጎልቶ የሚወጣበት ሊሆን ይገባዋል። የነፃነት ትግሉም መጀመሪያ ፍርሃትን ድል መንሳት ሊሆን ይገባዋል። ጣት ከመቀሳሰር ይልቅ እያንዳንደችን ለነፃነት ትግሉ ምን ይጠበቅብናል? ምንስ አበረከትን ብለን የምንጠይቅበት አመት ሊሆን ይገባዋል። የአዲሱ ዓመት ንጋት በኢትዮጵያ የዘወትር ርሃባችን የሆነው የነፃነትም ንጋት እንዲሆን ቀጠሮ ሳያስፈልግ ሁላችንም ለትግል በጽናት እንሰለፍ።

**ስለዚህ፡-**

**1ኛ/ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤**

የኢትዮጵያ ሕዝብ የገናና ስልጣኔዎች ባለቤት ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ የተገመደ የአንድነት ታሪክ ባለቤትም ነው፡፡ እጅ ለእጅ ተያይዞ ወራሪዎችን ድል በመንሳት ይታወቃል፡፡ አምባገነን ገዥዎችንም እንዲሁ፡፡ ሆኖም ችግሮቹ እያደር ተባብሰው ቀጥለዋል፡፡ የታመቀ የነፃነት ርሃብ ውስጡን ሞልቶታል፡፡ ነፃነቱን እውን ለማድረግ እንደሚችል ያለፈ ታሪኩ ምስክር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በአረቡ ዓለም እየተካሄደ ያለው የነፃነት ትግልና ውጤቱም ተግባራዊ ተሞክሮውን አጠናክሮለታል፡፡ ሕዝቡ ነፃ አውጭዎችን ቁጭ ብሎ የሚጠብቅበት ጊዜ አብቅቷል፡፡ እያንዳንዱ ሰው የነፃነቱ ባቤት ለመሆን አበክሮ ሊታገል ይገባል፡፡

**2ኛ/ ኢትዮጵያዊው ወጣት፤**

ወጣቱ ቀደም ባለው ጊዜ በነበረው የፖለቲካ ግብግብ ምክንያት አያሌ የተዛቡ ነገሮች ወራሽ ነው፡፡ በዚህ ዘመንም ያለው ዘርን መሠረት ያደረገ አገዛዝ ከኢኮኖሚ እስከ ማህበራዊ ፖሊሲዎቹ የወጣቱን ተስፋ የሚያለመልም ሳይሆን የሚያጨልም እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይኽንን የመሰለውን የተወሳሰበ ሁኔታ ፖለቲካዊ መፍትሔ እንዲያገኝ ወጣቱ ሲጠይቅም ምላሹ በገዛ አገሩ መጋዝ፣ መራብ መታረዝ፣ መታሰር፣ ስደትና ሞት ሆኗል፡፡ ወጣቱ እራሱን ከችግር ለመታደግ ይችል ዘንድ በአገዛዙ የሚቀርብለት አንድ አማራጭ ካለ እሱም የሥርዓቱን የአፈናና የችጋር ፖሊሲዎች ደግፎ እንዲቆም ነው፡፡ ይህን ጥሪ መቀበል ለጊዜው መፍትሔ ሊመስል ይችላል፡፡ የወደፊቷን የበለፀገችና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር ላለበት ኢትዮጵያዊ ወጣት ግን አምባገነን አገዛዝን ተሸክሞ መኖር ፈጽሞ አማራጩ ሊሆን አይችልም፡፡

የዘመናችን የኢትዮጵያ ወጣት ዛሬ ያለንበት ሁኔታ በልዩ ልዩ ችግሮች ተጠርነፎ ድንገት ሊገነፍል የሚችል ፀጥ ያለ ውቅያኖስ ነው፡፡ በሚማርበት ዘመኑ ጥራት ያለው ትምህርት እንዳያገኝ እድሉን ተነፍጓል፡፡ ሠርቶ አገሩን የሚያለማ ጉልበት ሲኖረው አገዛዙ ለ20 ዓመታት ሥራን መፍጠር አልቻለም፡፡ ይባስ ብሎም አገር ለቆ እንዲሰደድ ተሰዶም በባእድ እጅ የመከራ ገፈት እንዲጎነጭ ተፈርዶበታል፡፡ አገዛዙን ሲቃወም መፍትሔም ሲጠይቅ አደገኛ ቦዘኔ እየተባለ በሸዋሮቢትና ዝዋይ ወህኒ ቤቶች ፍዳውን ያያል፡፡ አገዛዙ ወጣቱን እንደ ቁጥር አንድ ጠላት ይመለከተዋል፤ በራሱም ሆነ በማንም ተስፋ የሌለው የአገዛዙ ዙፋን ጠባቂ እንዲሆንም ይሻል፡፡

ተስፋህ በእጅህ ነው፡፡ በውስጥህ ራስህን አይደለም አገርን ብሎም ትውልድን ሊለውጥ የሚችል እምቅ ኃይል አለ፡፡ የነፃት ህልምህን እውን ለማድረግ የመጀሪያው እርምጃ ፍርሀትን ድል መንሳት ነው፡፡ በ2004 ዓም የመጀመሪያዋ ቀን ጀምረህ ፍርሀትን ድል ንሳ፡፡ እንደ የቀደሙ ትውልዶች የለውጥ ሀዋሪያነት ዓርማህን አንሳ፡፡ ነፃነትህን ማንም እንዲሰጥህ አትጠብቅ፡፡ አንገትህን ከቀበርክበት ቀና አድርገህ ለህጋዊና ሠላማዊ ትግል እጅ ለእጅ ተያይዘህ ተንቀሳቀስ፡፡ አንድትነት ፓርቲ ከጎንህ ነው፡፡ 2004 ዓምን የትግልና የለውጥ ዓመት እንዲሆን አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ጥሪውን ከአክብሮት ጋር ያቀርብልሀል፡፡

**3ኛ/ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤**

በኢትዮጵያ በተለይም ከቅንጅት መፈረካከስ ጀምሮ ሕዝቡ ከፍተኛ ሀዘን ውስጥ ይገኛል፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የሕዝብን አጀንዳ ማስቀደም ሲገባን እርስ በርሳችን ባለመግባባትና በመለያየት ብዙ ጊዜ ማጥፋታችን ፈጾሞ ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ በአፈናና በርሃብ ክፉኛ እየተመታ ያለውን ሕዝባችንን አስቀድመን የተቀናጀ እና የተደራጀ ህጋዊና ሠላማዊ ትግል ልናደርግ ይገባናል፡፡ ከዚህ አንፃር በመድረክ በኩል እየታየ ያለው የመሰባሰብና ልዩነቶችን እያጠበቡ የመቀራረብ እንቅስቃሴ በጣም

የሚያስመሰግን ነው። ከዚህ በላቀ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ሀቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በመድረክ ዙሪያ በመሰባሰብ በጋራ ልንታገል ይገባናል። በገዥው ፓርቲ ቡራኬ የምትተዳደሩና ለገዥው ፓርቲ የጭቆና አገዛዝ ድጋፋችሁን ቀጥተኛ በሆነና ባልሆነ መንገድ እየሰጣችሁ የምትገኙ ‹‹ተቃዋሚ ፓርቲዎች›› ዛሬም በጣም ሳይረፍድ ከህዝብ ጎን እንድትቆሙ ጥሪያችንን በአንክሮ እናቀርባለን። በትክክለኛው የታሪክ ጎን እንድትቆሙ በተራበውና መብቶቹ በተረገጡበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**4ኛ/ ኢትዮጵያዊው ዲያስፖራ፤**

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዲያስፖራ ከሀገሩ ሳይወድ በግድ የራቀው በአፈና ምክንያት ነው። የተወሰነው ደግሞ በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ነው። ነገር ግን ከሀገሩ በአካል ቢርቅም በመንፈስ ፈጽሞ እርቆ አያውቅም። በተለይም በ1997 ምርጫ ምን ያህል ከሀገሩና ከወገኑ ጎን እንደቆመ በተግባር አስመስክሯል። ከ1997 ዓም በኋላ ግን የመቀዛቀዝና የወገኑን ስቃይ በውስጡ አምቆ በዝምታ መኖርን የመረጠ ይመስላል። ልዩ ልዩ እንቅስቃሴ የሚያደርገው የተወሰነውም ክፍልም ቢሆን የሚጠበቅበትን ያህል ኃይሉን አሰባስቦ እየታገለ አይደለም። እንዲያውም ቅንጦት በሚመስሉ ጉዳዩች ላይ አንዱ ሌላውን በማውገዝ ላይ የመጠመድና ጉልበትን በከንቱ የማዳከም ዝንባሌ ይታይበታል። ይህ በአስቸኳይ ሊቆም ይገባዋል። ዋናው የሁላችንም ትኩረት የነፃነት ጥያቄው ላይ መሆን አለበት። ይህ ጉዳይ ደግሞ የዲያስፖራውንም ተጠናክሮና ተደራጅቶ መውጣት የግድ ይላል። ኢትዮጵያውያን በያለንበት የነፃነት ጥያቄ አንድ ሊያደርገን እጅ ለእጅ ሊያይዘንም ይገባል። አገር ውስጥ የሚደረገው ትግል በከፍተኛ ሁኔታ በገንዘብ እጥረት የተመታ ነው። ስለዚህ ዳያስፖራው ሕዝቡና የተቃውሞው ጎራ እንዲተባበሩ ብሎም ለሕዝባዊ፤ ሠላማዊና ሕጋዊ ትግል እንዲነሳ ጥሪ ማድረጉ ተገቢም ወቅታዊም ነው። ነገር ግን ዲያስፖራው በበኩሉም የሚመዘንና የሚቆጠር የፖለቲካ፣ የፋይናንስና የዲፕሎማሲ ሥራ ሊሰራ ይገባዋል። በ2004 በዚህ መሰል እንቅስቃሴዎች ቢሰማራ አገር ውስጥ እንዲመጣ ለሚመኘው ለውጥ አንቱ የሚባል አስተዋፆ ያደርጋል ብሎ አንድነት ፓርቲ ያምናል።

**5ኛ/ ዓለማቀፉ ማህበረሰብ፤**

በኢትዮጵያ ያለው የአፈናና የኢኮኖሚ ድቀት ደረጃ በምንም አይነት መልኩ ክቡር ለሆነው የሰው ዘር የማይገባና ማንም ሊታገሰው የማይችል ነው። የዓለማቀፉ ማህበረሰብ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝብ ለነፃነቱ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በመደገፍ እያበረከተ ያለውን ገንቢ እንቅስቃሴ አንድነት ያደንቃል። ከዚህ በበለጠ ለዓለም አስተማማኝ ሠላማና የኢኮኖሚ መረጋጋት ለሆነው የሰው ልጅ ነፃነት ድጋፉን አጠናክሮ ሊቀጥልም ይገባል ይላል። የኢትዮጵያ ሕዝብም አሁን ካለበት የጭቆናና የችጋር አዙሪት እራሱን ነፃ ለማውጣት የሚያደርገውን የነፃነት ትግል ዓለማቀፉ ማህበረሰብ ከመቼውም ጊዜ በላቀ መልኩ ድጋፉን እንዲሰጥ አንድት ፓርቲ ጥሪውን ያቀርባል።

**6ኛ/ የኢህአዴግ አገዛዝ፤**

የኢህአዴግ አገዛዝ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ የተከሰተው ሕዝባዊና ሠላማዊ የለውጥ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ አይከሰትም የሚለውን የሞኝ ፈሊጥ በአስቸኳይ አቁሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ የለውጥ ጥያቄ ለማስተናገድ ብሎም በሀገራችን ሠላማዊና ሕጋዊ ለውጥ የሚያስተናግድበትን ሁኔታ ያመቻች። በእርግጥ በተጨባጭ እንደታየው ከሆነ አምባገነኖች ከአጠገባቸው ካሉ አምባገነኖች እንኳን የመማር ብቃታቸው እጅግ አንስተኛ እንደሆነ ነው። መገለጫቸውም መማር አለመቻላቸው ነው። በኢትየጵያችን ይህ እንዳይሆን አበክረን እንመክራለን። በሌላው በኩል ደግሞ ሚሊዮኖች በርሃብ በሚሰቃዩበትና ልመና መገለጫችን በሆነበት ሀገር የኢትዮጵያ ሕዝብ ልማቱ ስለተረጋገጠለት እንደ አረብ አገሮች ለነፃነቱ አይነሳም የሚለው የሞኝ ፈሊጥ አንድም የኢትዮጵያን ሕዝብ አገዛዙ በጣም እንደሚንቅ የሚሳብቅ ሲሆን በሌላ በኩል በአረብ አገራት ያለውን የኢኮኖሚ አቅም በቅጡ ለማገናዘብ እየቻለ ቅጥፈትን እንደመውጫ መንገድ የሚወስድ አገዛዝ መሆኑን ነው። ከእንዲህ አይነት ወንዝ

የማያሻግር የማደናገሪያ ታክቲክ በመውጣት ለተጨባጭ የሕዝብ ጥያቄዎች ተጨባጭ ምላሽ አሁኑኑ ለመስጠት ይዘጋጅ። ሕዝብ መብቱን ለማስከበር ሠላምን አደፍርሶ አያውቅም አሁንም ነፃነቱን ከማስከበር ውጭ የሀገሩን ሠላም እንደማያደፈርስ እሙን ነው። አገዛዙም ለሕዝብ ሠላማዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ሠላማዊ ምላሽ ቢሰጥ ከምንም በላይ ለራሱ፣ ለሕዝብ ለሀገርና ለትውልድ ጠቃሚና ክቡር ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል ብሎ አንድነት ያምናል።

በመጨረሻም እያንዳንዱ ሰው ለሁሉም፤ ሁሉም ለእያንዳንዱ መብት እጅ ለእጅ ተያይዞ በ2004 ዓም በአንድነት ለትግል እንዲንቀሳቀስ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ጥሪውን እያቀረበ 2004 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍርሃት የሚላቀቅበት ከችጋር ነፃ የሚወጣበት ነፃነቱን የሚጎናፀፍበት አንድነቱና ሠላሙን የሚያጠነክርበት ዓመት እንዲሆን አንድነት ታላቅ ምኞቱን ከአክብሮት ጭምር ይገልፃል።

መልካም አዲስ ዓመት!
መልካም የነፃነት ትግል!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
ጳጉሜ 4 ቀን 2003 ዓም
አዲስ አበባ